## ክፍያ ያለው የህመም እና ደህንነት ዕረፍት ጊዜ እና COVID-19 -- በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶች

ሰራተኞች ክፍያ ያለው የህመም እና ደህንነት ዕረፍት ጊዜ (PSST) መጠቀማቸውን በማረጋገጥ አሰሪዎችና ሰራተኞች የማህበረሰቡን ደህንነትና ጤንነት ለማስጠበቅ የድርሻቸውን መወጣት ይችላሉ። ይህ ሰነድ የሲያትል ክፍያ ያለው የህመም እና የደህንነት ዕረፍት ጊዜ ሕግን በተመለከተ እርስዎ ለሚኖሩዎት ጥያቄዎች መልሶችን ይሰጣል። ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እባክዎ የ[ሠራተኞች ደረጃዎች ቢሮ (Office of Labor Standards)] ድረ ገጽን ይጎብኙ።

ክፍያ ያለው የህመም እና የደህንነት ዕረፍት ጊዜ መመሪያ (Paid Sick and Safe Time):-

- ሰራተኞችና ልጆች በሚታመሙበት ወቅት ቤት ውስጥ መቆየታቸውን፣ ከሌሎች ሰራተኞች፣ ከትምህርት ቤትና ከደንበኞች መራቃቸውን በማረጋገጥ የማህበረሰብ ጤናን ያስጠብቃል
- የበሽታን ስርጭት በመገደብ ይበልጥ ምርታማ የሆኑ የስራ ቦታዎችን ይፈጥራል
- ሰራተኞች ደመወዛቸውን ሳያጡ ጤንነታቸውን መንከባከብ ስለሚችሉ፣ ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን ይገነባል

---

ክፍያ ያለው የህመም እና ደህንነት ዕረፍት ጊዜ (PSST) **ምንድን ነው?**
ክፍያ ያለው የህመም እና ደህንነት ዕረፍት ጊዜ አሰሪው ለሰራተኞች ከክፍያ ጋር የሚሰጠው የእረፍት ጊዜ ሲሆን፣ ሰራተኞችም ይህን እረፍት ለሚከተሉት ጉዳዮች መጠቀም ይችላሉ:-

- ራሳቸው ወይም የቤተሰባቸው አባል ሲታመም፣ ሲጎዳ ወይም የጤና ችግር ሲያጋጥመው ለመንከባከብ
- የሕክምና ወይም የቅድመ መከላከያ እንክብካቤ ለማግኘት ወደ ሐኪም ለመሄድ
- የስራ ቦታቸው በጤና ጉዳዮች ምክንያት በመንግስት ባለስልጣን ትእዛዝ ሲዘጋ
- የልጃቸው ትምህርት ቤት ወይም የእንክብካቤ ቦታ በጤና ጉዳዮች ምክንያት በመንግስት ባለስልጣን ትእዛዝ ከተዘጋ

**PSST የሚያገኙ ሰራተኞች የትኞቹ ናቸው?**
Seattle ውስጥ፣ አሰሪዎች ለሁሉም ሰራተኞች ክፍያ ያለው የህመም እና ደህንነት ዕረፍት ጊዜ እንዲሰጡ ሕጉ ያስገድዳል። በዚህም ውስጥ የሚካተቱት የሙሉ ጊዜ፣ የትርፍ ጊዜ፣ የሚታለፉና የማይታለፉ ሰራተኞች ናቸው።

**ሰራተኞች ምን ያህል PSST ያገኛሉ?**
ክፍያ ያለው የህመም እና ደህንነት ዕረፍት ጊዜ በጊዜ ሂደት የሚገኝ ነው። መጠኑ የሚመሰረተውም አንድ ሰራተኛ በሰራበት የስራ ሰዓትና በአሰሪያቸው የንግድ ስራ ዓይነት ላይ ነው። ለዝርዝር መረጃ፣ የ[ሠራተኞች ደረጃዎች ቢሮ] ድረ ገጽ ይጎብኙ።

**አንድ ሰራተኛ በአንድ ጊዜ መውሰድ የሚችለው ምን ያህል PSST ነው?**
አንድ ሰራተኛ በጊዜ ሂደት የተጠራቀመለትንና የተጨመረለትን ሰዓት መጠን በተቻለ መጠን ዝቅተኛውን መጠቀም ያለበት ሲሆን፣ ይህም አሰሪው የስራ ሰዓትን ለመከታተል እንዲያመቸው ነው (ከአንድ ሰዓት ግን መብለጥ የለበትም)።

**አንድ ሰራተኛ የ PSST ቀሪ ሂሳቡን እንዴት ማግኘት ይችላል?**
አሰሪዎች ደመዎዝ በከፈሉ ቁጥር ይህን መረጃ ማጋራት አለባቸው። በርካታ አሰሪዎች ይህን መረጃ የክፍያ ቁራጩ ላይ ይጽፉታል ወይም በኦንላይን የፔይሮል መረጃ ስርዓት ላይ እንዲታይ ያደርጉታል።

**አንድ ሰራተኛ <u>የስራ ቦታው፣</u> <u>የልጁ ትምህርት ቤት፣</u> <u>የልጁ የእንክብካቤ ቦታ</u> እንደ COVID-19 ባለ የጤና ችግር ምክንያት በመንግስት ባለስልጣን ቢዘጋ፣ PSST መጠቀም ይችላል?**
<u>አዎ</u>። አንድ ሰራተኛ የስራ ቦታው፣ የልጁ ትምህርት ቤት፣ የልጁ የእንክብካቤ ቦታ ከመንግስት ባለስልጣን ትእዛዝ ሳይሰጥ ቢዘጋ፣ ሰራተኛው የተጠራቀመ PSST እንዲጠቀም አሰሪው ሊፈቅድለት ይችላል። ለምሳሌ፣ የአንድ የግል ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር (የመንግስት ባለስልጣን ያልሆነ) የሰራተኛውን ልጅ ትምህርት ቤት ቢዘጋ፣ አሰሪው የራሱን ምርጫ በመውሰድ ሰራተኛው የተጠራቀመ PSST እንዲጠቀም ሊፈቅድለት ይችላል።

**የመንግስት ባለስልጣን ማነው?**
የመንግስት ባለስልጣን ማለት የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ የስራ ቦታ ወይም ትምህርት ቤትን የመዝጋት ስልጣን የተሰጠው ነው። በዚህም ውስጥ፣ የአካባቢ፣ የግዛት ወይም የፌዴራል ባለስልጣናትና የማህበረሰብ ጤና ሃላፊዎች (ለምሳሌ ሲያትል- ኪንግ ካውንቲ የወረዳ የሕዝብ ጤና (Seattle - King County Public Health)፣ የበሽታ ቁጥጥር ማዕከል (Center for Disease Control) ወይም የግዛት ጤና ክፍል (State Department of Health) ወይም የሕዝብ ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ወይም ርዕሰ መምህር ይካተታሉ።

**አሰሪዎች አንድ ሰራተኛ PSST ለምን እንደሚጠቀም ዝርዝር መረጃ መጠየቅ ይችላሉ?**
<u>አይችሉም</u>። ሰራተኞች PSST የሚጠቀሙበትን ምክንያት የማጋራት ግዴታ የለባቸውም። አሰሪዎች ለ PSST ከተፈቀደው ሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ ሰራተኛው ከስራ ከቀረ ምክንያቱን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቁ ይችላሉ።

በዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረበው መረጃ እንደ ህጋዊ ምክር የታሰበ አይደለም እናም ለህጎች እና መመሪያዎች ምትክ ሆኖ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም።

**አንድ ሰራተኛ PSST እንዲጠቀም ማስገደድ ይችላሉ?**
አይችሉም። አሰሪዎች በሕጉ በሌላ መልኩ ለሚሸፈን ከስራ መቅረት ሰራተኞች PSST እንዲጠቀሙ ማስገደድ አይችሉም።

**አሰሪው የታመመ ሰራተኛ ወደ ቤት እንዲሄድ ማስገደድ ይችላል?**
የ PSST ሕግ አሰሪው የታመመ ሰራተኛውን ወደ ቤት ከመላክ አይከለክለውም። አንድን ሰራተኛ ወደ ቤት መላክ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን የሚወስኑትለሌሎች የግዛት እና የአካባቢ ሕጎች ናቸው። ለምሳሌ፣ የ ግዛት ጤና ክፍል ደንቦች አንድ የምግብ አገልግሎት ሰራተኛ እንደ ትውከት ያሉ ምልክቶች ወይም ትኩሳት ያለበት የቆሰለ ጉሮሮ ያለበትን ሰራተኛ አሰሪው ወደ ቤቱ መላክ እንዳለበት ይደነግጋሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ [Washington Administrative Code 246-215] ይመልከቱ ወይም ለ [ሲያትል- ኪንግ ካውንቲ የወረዳ የሕዝብ ጤና] ያሳውቁ።

**አንድ ሰራተኛ ወረርሽኝ ወደተቀሰቀሰበት ሃገር ደርሶ በመምጣቱ ምክንያት አሰሪው እንዳይሰራ ሊከለክለው ይችላል?**
ወደ አንድ የተወሰነ ሃገር ወይም ክልል ጉዞ ማድረግ አንድ ሰው ለ COVID-19 ስለመጋለጡ አስተማማኝ ጠቋሚ አይደለም። ለ COVID-19 ወረርሽኝ መቀስቀስ ወይም መንስኤነት አንድ የተወሰነ ቡድን በተለይ ዒላማ መደረግ የለበትም። አድሎንና የተዘባ መረጃ ስርጭትን እንዴት መከላከልና ምላሽ መስጠት እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት [እዚህ ላይ ጠቅ ያድርጉ]። በአንድ ሰራተኛ የብሔር ማንነት ወይም የመጣበት ቦታ ላይ ተመስርቶ አሉታዊ የሆነ የስራ ቅጥር እርምጃ መውሰድ አድሎ ወይም ልዩነት በማድረግ ሊያስጠይቅ ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ፣ [Office of Civil Rights] በስልክ ቁጥር 206-684-4500 ያነጋግሩ።

**አንድ ሰራተኛ የተጠራቀመ PSST ከተጠቀመ ወይም የተጠራቀመ ፈቃድ የሌለው አዲስ ሰራተኛ ከሆነስ?**
አንድ አሰሪ ሰራተኛው እንዲጠቀም የሚፈቅድለት የተጠራቀመ የ PSST ሰዓቱን ብቻ ነው። አሰሪዎች በራሳቸው ውሳኔ መሰረት ተጨማሪ ፈቃድ ከክፍያ ጋር ሊሰጡ ወይም የሽርሽር ጊዜ ወይም የተጠራቀመ ፈቃዳቸውን እንዲጠቀሙ ሊፈቅዱ ይችላሉ። ሌሎች ሕጎችም አሰሪው ለሰራተኞቹ ፈቃድ እንዲሰጥ ይጠይቃሉ፤ እነርሱም፦ የቤተሰብ እና የሕክምና እረፍት ሕግ (Family and Medical Leave Act)፣ የዋሽንግተን ግዛት ክፍያ ያለው የቤተሰብ ሕክምና ዕረፍት ጊዜ (Washington State Paid Family Medical Leave) እና የፌዴራል፣ የግዛትና የአካባቢ የአካል ጉዳተኞች ሕጎች ናቸው።

**አንድ ሰራተኛ ያልተጠቀመበትን PSST ወደ ክፍያ ያለው ፈቃድ ልገሳ ዕቅድ በመለገስ PSST የሚያስፈልጋቸውን የስራ ባልደረቦቹን ማገዝ ይችላል?**
አዎ፣ አሰሪው ይህን የሚፈቅድ ፕሮግራም ካለው። (ሕጉ ይህን እንዲያደርግ አያስገድድም።)

**አንድ ሰራተኛ PSST ለመውሰድ የሚያስፈልገውን ሰዓት የሚሸፍንለት ሌላ ሰው መፈለግ አለበት?**
የለበትም። አሰሪው ሰራተኛው የ PSST ሰዓቱን የሚሸፍንለት ሌላ ሰው እንዲፈልግ ማስገደድ አይችልም።

**ሰራተኛው paid sick እና safe time ከመጠቀም ይልቅ ፈረቃዎችን መለዋወጥ ይችላል?**
አዎ። አሰሪውና ሰራተኛው ከተስማሙ፣ ሰራተኛው PSST ከመውሰድ ይልቅ ፈረቃዎችን መለዋወጥ ይችላል።

**የሲያትል መንግስት ትምህርት ቤቶች (SPS, Seattle Public Schools ) ሰራተኞች በ Seattle Paid Sick እና Safe Time ሕግ ይሸፈናሉ?**
አይሸፈኑም። ነገር ግን፣ አንዳንድ የ SPS ሰራተኞች በ Washington ግዛት Paid Sick Leave ሕግ ሊሸፈኑ ይችላሉ። ስለ ግዛት ጥበቃዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡ https://lni.wa.gov/workers-rights/leave/paid-sick-leave/።

**አንድ ሰራተኛ በሕግ ጥበቃ ከተሰጣቸው ምክንያቶች ውጭ ላሉ ምክንያቶች PSST መጠቀም ይችላል?**
አዎ። አሰሪው በሕጉ ላልተሸፈኑ ጉዳዮች PSST መጠቀምን ሊፈቅድ ይችላል።

**በዚህ ሕግ ስር የተሰጡ መብቶች ወይም ግዴታዎችን በተመለከተ ተጨማሪ ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማንን ደውዬ ማናገር እችላለሁ?**
እባክዎ ለ ሠራተኞች ደረጃዎች ቢሮ (OLS) በስልክ ቁጥር 206-256-5297 ይደውሉ ወይም ቀጣዩን ድረ ገጻችንን ይጎብኙ፡ http://www.seattle.gov/laborstandards። ጥያቄዎችዎን ልንመልስና የመረጃ ግብዓቶችን ልናቀርብ እንችላለን።

**ስለ COVID-19 (ከዚህ በፊት ኖቭል ኮሮናቫይረስ የሚባለው) እና ለመዘጋጀት መውሰድ ስለምችላቸው እርምጃዎች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው የት ነው?**
ለተጨማሪ መረጃ፣ የ ሲያትል- ኪንግ ካውንቲ የወረዳ የሕዝብ ጤና ድረ ገጽን በመጎብኘት ስለ COVID-19 የተዘጋጀውን [የመረጃ ቅጻቸውን] ማየት ይችላሉ፤ ይህም በተገጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችንና ለአጠቃላዩ ሕዝብ፣ ለትምህርት ቤቶች፣ ለስራ ቦታዎችና ለጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ዝግጁነት የሚሆኑ ምክረ ሃሳቦችን በስፋት የያዘ ነው።

በዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረበው መረጃ እንደ ህጋዊ ምክር የታሰበ አይደለም እናም ለህጎች እና መመሪያዎች ምትክ ሆኖ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም።